# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# ንጉሱ ዳዊት
# (ክፍል ሁለት)

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



ዳዊት በደቡብ እስራኤል የይሁዳ ንጉስ ነበረ፡፡ ነገር ግን የተቀረው የእስራኤል ክፍል የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴን ንጉስ አድርጎ ወስዶት ነበረ፡፡ ለሰባት አመታት የእርስ በርስ ጦርነት ነበረ፡፡ ነገር ግን ዳዊት ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥንካሬው ይጨምር ነበረ፡፡




በመጨረሻም ፣ ንጉስ ኢያቡስቴ በሁለት
የገዛ ራሱ ወታደሮች ተገደለ፡፡




3

ከዚያም ሁሉም የእስራኤል ነገድ ወደ ዳዊት መጥቶ በእስራኤል ላይ ንጉስ
አድርጎ ቀባው፡፡ በስተመጨረሻም ፣ ዳዊት የሀገሩ ሁሉ ንጉስ ሆነ፡፡




4

ንጉስ ዳዊት ያደረገው የመጀመሪያው ነገር እየሩሳሌምን መያዝ ነበረ፡፡ የዳዊት
ከተማም ተባለች፡፡ ከጠላት ይልቅ ጠንካራ እንድትሆን አድርጎ ገንብጸቷት
ነበረ፡፡ ከኢየሩሳሌምም ፣ የዳዊት ሰራዊት ፍልስጤማዊያንና ሌሎች የእስራኤል
ጠላቶችን ለማሸነፍ ተነስቶ ወጣ፡፡



5

በመቀጠልም ፣ ንጉስ ዳዊት
የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ
እየሩሳሌም ይዞት መጣ፡፡
የእግዚአብሔር ታቦትም
አስርቱን ትዕዛዛትና ሌሎችንም
በሙሴ እጅ የተሰጡትን ሌሎች
ትዕዛዛት የያዘ ነበረ፡፡ ታቦቱም
፣ እስራኤላዊያንን ስለ
እግዚአብሔር ቅድስና እና
ለእርሱ እንዴት መገዛት
እንዳለባቸው ያዛል፡፡



6

በንግስናው የመጀመሪያ አመታት
ዳዊት ብዙ ጦርነቶችን መጋፈጥ
ነበረበት፡፡ እርሱም ብልህ ጦረኛ እና
የእግዚአብሔርን ምሪት የሚጠይቅ
ትሁት ሰው ነበረ፡፡



7

ዳዊትም ፣ የእግዚአብሔር
ታቦት በድንኳን ተቀምጦ ፣
እርሱ በጥሩ ቤት ውስጥ መኖሩ
እጅግ ያስጨንቀው ነበረ፡፡
ዳዊትም ቤተመቅደስን ሊሰራ
አሰበ፡፡ የእግዚአበሔር
ነብይ የሆነው ናታን
ከፊቱ ቀድሞ
እንዲሄድ ለመነው፡፡



8


ያንን ምሽት ፣ እግዚአብሔር ለዳዊት መልዕክትን ላከለት፡፡ “አገልጋዬ ዳዊት ሆይ ፣ እግዚአብሔር ቤትን ይሰራልሃል፡፡” ዘመንህ ሲፈጸምና ከአባቶችህጋ ስትከማች ፣ ልጅህን ከአንተ በኋላ የሚሆን ንጉስ አደርገዋለሁ፡፡ ለስሜ ቤትን ይሰራልኛል ፤ እኔም የንግስናውን ዙፋን ለዘላለም አጸናለታለሁ፡፡
9


ዳዊትም ከሳኦል ቤተሰብ የተረፈ ካለ እርዳታን ሊያደርግለት ፈለገ፡፡ የዮናታን ልጅ የሆነውን ሜምፊቦስቴን ብቻ አገኘው ፤ እርሱም አካለ ስንኩል ነበረ፡፡ ዳዊትም አለ ፣ “በጠረጴዛዬ ላይ እንደ ንጉስ ልጅ አብሮኝ ይበላል፡፡” ዮናታን ውድ ጓደኛው ስለነበረ ፣ ዳዊት ለሜምፊቦስቴ እጅግ መልካም ሰው ነበረ፡፡
10


ዳዊት እግዚአብሔርን በታዘዘውና በታመነው መጠን ፣ እግዚአብሔር አበለጠገው፡፡ ነገር ግን ፣ አንድ ቀን ፣ የሚያስፈራ ጥላ በዳዊት ሕይወት ላይ ተጋረደ፡፡ አንድ ሌሊት ፣ መተኛት አልቻለም፡፡ በሰገነት ላይ ይመላለስ ነበረ እና ከተማውንም ይመለከታል፡፡
11


ዳዊትም ቆንጆ ሴት በሰገነት ላይ ስትታጠብ አየ ፤ ስሟም ቤርሳቤህ ይባላል፡፡ ምንም እንኳን የቤርሳቤህ ባል ኦርዮ ለዳዊት የተወደደ ወታደር ቢሆንም ፣ ከቤርሳቤህጋ ኃጢያትን አደረገ፡፡ ቤርሳቤህ ልጅ ልትወልድለት እንደሆነ ሲሰማ ፣ ዳዊት ኃጢያቱ ሌላ ብዙ መዘዝ ሊያመጣ እንደሆነ አስተዋለ፡፡
12


ወደ እግዚአብሔር ከመናዘዝ ይልቅ ፣ ዳዊት ኃጢያቱን መሸፈንን መረጠ፡፡ ይሔ በፍጹም ሊሰራ አልቻለም፡፡ እየመጣ ያለው ሕጻን የእርሱ እንደሆነ እንዲያስብ ፣ ኦርዮንን ከውጊያ ቦታ አስጠርቶ ፣ ወደቤቱ ላከው፡፡ አብረውት ያሉ ጦረኞች ለጦርነት ውጪ ሆነው ፣ ኦርዮ ቤቱ ውስጥ መቅረት አልፈለገም፡፡ ኦርዮ በንጉሱ ደጅ ተኛ፡፡
13



በዚህም ፣ ዳዊት እጅግ የከፋ ነገር አደረገ፡፡ ኦርዮን ወደ ጦሩ ሜዳ ደብዳቤ አስይዞ ላከው፡፡ ደብዳቤው በጦሩ ሜዳ ላይ ኦርዮ እንዲገደል ብሎ ጀነራሉን የሚያዝ ጽሑፍ ነው፡፡ ኦርዮ ሲገደል ፣ ዳዊት ቤርሳቤህን ሚስቱ አድርጎ ይወስዳታል፡፡
14

እግዚአብሔር አገላጋዩ ናታንን ለዳዊት ኃጢያቱን እንዲያመለክት አዝዞት ላከው፡፡ ናታን ለዳዊት ስለ አንድ ባለጠጋ እና ደኃ ሰው ታሪክ ነገረው፡፡ ባለጠጋው ሰው በመቶዎች የሚቆጠሩ በጎች አሉት፡፡ ነገር ግን ፣ ደኃው ሰው ግን እንደ ልጁ የሚያያት ፣ አንዲት ጠቦት ብቻ ነበረችው፡፡




15

አንድ መንገደኛ ወደ ባለጠጋው ሰው ሲመጣ ፣ ባለጠጋው ሰውዬ ከራሱ ወስዶ ካሉት ጠቦቶች መሃከል አንዷን ወስዶ ሊያርድለት አልፈለገም፡፡ ነገር ግን ፣ የደኃውን ያቺን አንዷን ጠቦት ወስዶ አረዳት፡፡




16

ዳዊት በባለጠጋው ሰው ራስ ወዳድነት እጅግ ተናድዶ ነበረና አለቀሰ፡፡ ፣ “ይህንን ያደረገው ሰው በእርግጥ መገደል አለበት” አለ፡፡



17

ጠቢብ የሆነው ናታን እንዲህ አለው ፣ “ያ ሰው አንተ ነህ!”፡፡ ዳዊት ያደረገው ነገር ባለጠጋው ሰውዬ በታሪኩ ውስጥ ካደረገው ነገር ይበልጣል፡፡



18

እግዚአብሔር ዳዊት እንዴት ክፉ እንደነበረ አሳየው፡፡ ዳዊትም በኃጢያቱ እጅግ አዘነ፡፡ እርሱም “አንተን ብቻ በድዩ ፣ይሔንን ክፉ ነገር አደረግኩኝ፡፡” እግዚአብሔርም የዳዊትን ኃጢያት ይቅር አለው፡፡ ነገር ግን የቤርሳቤህ ልጅ ታመመ ፤ እንደተወለደም ሟተ፡፡



19

እግዚአብሔር ዳዊትን ስለ ከፋ ኃጢያቱ ይቅር አለው፡፡ ቤርሳቤህ ሌላ ልጅ ወለደች ፤ ሰሎሞን የሚባል ፤ ከዳዊት በኋላ ታላቅ የሆነ ንጉስ ነበረ፡፡ ነገር ግን ንጉስ ዳዊት ሌሎች ብዙ ልጆች ነበሩት ፤ አንዳንዶቹ እጅግ የሚያሳዝኑት ነበሩ፡፡



20


ንጉሡ ዳዊት ( ክፍል ሁለት)

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ሳሙኤል 1 - 12

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት 119:130**






21 60



ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16